የግቢ ጉባኤያት የቅድመ ምረቃ ሥርዓተ ትምህርት

ክርስትያናዊ ሕይወትና ሥነምግባር

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ማኅበረ ቅዱሳን ትምህርትና ሐዋርያዊ አግልግሎት ዋና ክፍል የተዘጋጀ

መስከረም 2005

መርሐ ትምህርት

የትምህርት ዓይነት፦ ክርስቲያናዊ ሕይወትና ሥነ ምግባር

መለያ ቁጥር፦ ክሕሥ 123

መግቢያ፦ ክርስቲያናዊ ሕይወትና ሥነ ምግባር ትምህርት ተማሪዎቹ መሠረተ እምነታቸውን የሚረዱበትን የነገረ ሃይማኖት ትምህርት እንደጨረሱ የሚማሩት መሠረታዊ ትምህርት ነው።።በቅዱስ መጽሐፍ አንድ ሰው ለመዳን እምነትን ከሥራ ጋር ማስተባበር እንዳለበት በተገለጸው መሠረት ተማሪዎች በዚህ የክርስቲያናዊ ሕይወትና ሥነ ምግባር ትምህርት ሕይወቱን እንዲኖሩት ለማስቻል መምህሩ የተማሪዎቹን የመንፈሳዊ ሕይወት ደረጃ በመገንዘብ ትምህርቱን አሳታፊ በሆነ መንገድ ለማስተላለፍ መዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል።የትምህርቱ መሠረታዊ ትኩረት ሥነ ምግባር ምን እንደሆነ ፣ ከድኅነት አንጻር ያለውን ጠ ቀሜታ፣ የዐሥርቱ ትዕዛዛት እና ስድስቱ ቃላተ ወንጌልን ፋይዳ ማስገንዘብ ነው። ከዚህም ባሻገር ተማሪዎች የመንፈሳዊ ሕይወት መገለጫዎች የሆኑትን የመንፈስ ፍሬዎች ቀስ በቀስ እንዲለማመዱና እንዲኖሩባቸው ማስገንዘብ ላይ ያተኩራል። በተጨማሪም የመንፈሳዊ ተጋድሎ መንገዶች የሆኑ ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት፣ ምጽዋትን በማስተዋል ይፈጽሙት ዘንድ እንዲሁም ክርስትና ከራስ አልፎ ለሌላውም ማሰብ ስለሆነ በማኅበራዊ ሕይወትም ሊኖራቸው የሚገባው ሱታፌ ክርስቲያናዊ እንዲሆን የሚያደርግ ግንዛቤ መፍጠርን ማእከል ያደረገ ነው። በአጠቃላይ ተማሪዎች ይህን ትምህርት በመማራቸው ራሳቸውን በተገቢው ክርስቲያናዊ ሕይወት አንጸው እንዲኖሩ በዚህም የመንግሥቱ ወራሾች እንዲሆኑ ማብቃት ላይ ባተኮረ ሁኔታ ማስተማር ይገባል።።

ምዕራፍ አንድ፦ የክርስቲያናዊ ሕይወትና ሥነ ምግባር ትምህርት መግቢያ

የምዕራፉ አጠቃላይ ውጤት፦ ተማሪዎች ይህንን ምእራፍ ከተማሩ በኋላ

- የክርስቲያናዊ ሕይወትን ምንነት ይገነዘባሉ።
- በነገረ ድኅነት የምግባርን አስፈላጊነት አምነው ይቀበላሉ።
- የመልካም ምግባርን ጽንሰ ሀሳብ ይረዳሉ።
- የሰብአዊ እና ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን ልዩነትና አንድነት ይገነዘባሉ።

የሚጠበቅ ብቃት/ /	ይዘት / /	የመማር ማስተማር ክንውን / / እና ዘዴዎች /ግብዓቶች
• የክርስቲያናዊ ሥነ ምግባርን ጽንሰ ሀሳብ ያብራራሉ	1.1 ክርስቲያናዊ ሕይወትና ምግባር ምንነት	በዚህ የመግቢያ ትምህርትየትምህርቱን ምንነትና አጠቃላይ ዓላማ ከገለጹ በኋላ በእናንተ መረዳት ጥሩ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር አለው ብላችሁ የምታስቡት ምን ዓይነት ሰው ነው?የሚል ጥያቄ በመጠየቅ መጀመር፤ከዚያም የምግባር ምንነትን በመግለጽ በጽንሰ ሐሳቡ መሠረት በተግባር እያከናወኑ መኖር ክርስቲያናዊ ሕይወት እንደሆነ ያብራሩ። በመቀጠልም አንድን ምግባር ክፉና ደግ የሚያሰኘው ምኑ ነው ? በሚል ተማሪዎችን በማሳተፍ የተወሰኑ ተማሪዎችን ከጠየቁ በኋላ መልካም ምግባር የሚመነጨው ከእምነትና ፍቅር መሆኑን በማስረገጥ ማብራሪያ ይስጡ።
• ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር የሚመነጨው ከእምነትና ከፍቅር መሆኑን ይገልጻሉ።	1.2. ክርስቲያናዊ ሕይወትና ምግባር ከምን ይመነጫል ?	
• በነገረ ድኅነት የምግ ባርን አስፈላጊነት ያስረዳሉ • ለመዳን ሃይማኖትን ከምግባር ጋር ማስተባበር አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝበው መልካም ምግባር ለመሥራት ይተጋሉ	1.3. በነገረ ድኅነት የምግባር አስፈላጊነት	በነገረ ድኅነት ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ያዳነን በቸርነቱ ስለመሆኑ አንዳንድ ነጥቦችን ካነሱ በኋላ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው በሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል በመነሣት መምህሩ በቂ ማብራሪያ ይስጡ። አያይዘውም የምግባርን አስፈላጊነትና የእግዚአብሔርን ቸርነት እንዴት መረዳት እንደሚገባ ያስገንዝቡ።

የሚጠበቅ ብቃት	ይዘት	የመማር ማስተማር ክንውን እና ዘዴዎች /ግብዓቶች
• የሰብአዊ ሥነ ምግባር እና ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር አንድነትና ልዩነት ይተነትናሉ	1.4. ሰብአዊ ሥነ ምግባርና ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር	ትምህርቱ እንደሚሰጥበት ግቢ ጉባኤ አካባቢያዊ ሁኔታ መነሻ የሚሆኑ ምሳሌያዊ ማሳያዎችን/ሴናሪዮስ/ በማቅረብ የሥነ ምግባርን ስፋትና ጥልቀት ካሳዩ በኋላ አንድን መልካም ምግባር ሰብአዊ ወይም ክርስቲያናዊ የሚያሰኘው ምን እንደሆነ በማመልከት ያስረዱ። በመጨረሻም መልካም ምግባር ሠርተው የተመሰከረላቸውን ቅዱሳንን በመጥቀስ፣ በነገረ ድኅነት የምግባርን ወሳኝነት አጉልቶ በማውጣት እንዲሁም በሌላ እምነት የሚነሱትን ምግባርን የተመለከቱ ጥያቄዎች አንስቶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማሰረጃ በማቅረብ ትምህርቱን ማጠቃለል ይገባል።

ምዕራፍ ሁለት፡- የክርስቲያናዊ ሕይወትና ምግባር መሠረቶች (3 ሰዓት)

ከተማሪዎች የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት / /

- ሕግጋተ እግዚአብሔርን ይገነዘባሉ
- ያክርስቲያናዊ ሕይወት መሠረቶችን ተረድተው በሕይወታቸው ለመተርጎም ይነሳሳሉ

የሚጠበቅ ብቃት	ይዘት	የመማር ማስተማር ክንውን
• ዐሥርቱ ቃላተ ኦሪትን ይዘረዝራሉ • የኢያንዳንዱን ምሥጢር ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ ያብራራሉ • ዐሥርቱ ቃላት ለክርስቲያናዊ ሕይወት ያላቸውን ሚና ይተነትናሉ • ዐሥርቱ ትዕዛዛትን ምን ያህል እየፈጸሙ እንደሆነ ራሳቸውን ይገመግማሉ	2.1 ዐሥርቱ ቃላተ ኦሪት	ይህን ክፍለ ትምህርት ለማስተማር 90 ደቂቃ ይጠቀሙ፡፡ የሚለተለውን ጥያቄ በመጠየቅ መጀመር ይችላሉ፡፡ • ትዕዛዛት/ህግጋተ እግዚአብሔር / ለሰው ልጅ ለምን አስፈለገ? የዚህን ጥያቄ መልስ እያንዳንዱ ተማሪ በማስታወሻ ደብተሩ ላይ እንዲጽፉ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም የተወሰኑ ተማሪዎችን ተራ በተራ እያስነሱ የጻፉትን መልስ እንዲያነቡ ያድርጉ በመጨረሻ ከተነበቡት የተለየ ሀሳብ ያለው ተማሪ ካላ እድል ይስጡና ትዕዛዛት ለሰው ልጅ ለምንና እንዴት እንደተሰጡ በማብራራት ያጠቃልሉ፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎችን በአስር ምድብ በመክፈል ለእያንዳዱ ምድብ ከዐሥርቱ ትዕዛዛት አንዱን በመስጠት ተወያይተው ትርጉሙና ምሥጢሩ ምን እንደሆነ እንዲያቀርቡ ያድርጉ /ወይንም ደግሞ ከዚህ ክፍለ ግዜ አስቀድሞ በየቤት ሥራ መልክ መስጠትም ይቻላል/፡፡ ተማሪዎች ባቀረቡት ላይ ማስተካከያ በመስጠትና አሁን ካለው ተጨማጭ ሁኔታ እና ከሕይወታቸው ጋር በማዛመድ የእያንዳንዱን ትዕዛዝ ትርጉምን ምሥጢር ያብራሩ፡፡ ለምሳሌ አትግደል የሚለው ትዕዛዝ የሌላውን ሰው ነፍስ ማጥፋት ብቻ ሳይሆን አንድ ሰው ንስሃ ካልገባ ነፍሱን እየገደለ መሆኑን ወዘተ . . .፡፡ እያንዳንዱ ተማሪ ከትዕዛዛቱ አንጻር ሕይወቱን እንዲገመግም ያበረታቱ፡፡
2.2 የተራራው ስብከትና ሌሎች የወንጌል ሕግጋት		
		የህንን ክፍለ ትምህርት ለማስተማር 90 ደቂቃ ይጠቀሙ፡፡

• የወንጌል ሕግጋትን/6ቱ ቃላተ ወንጌልን/ ይዘረዝራሉ • የእያንዳንነዱን ሕገ ወንጌል ምሥጢር ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ ያብራራሉ • የወንጌል ሕግጋትን ምን ያህል እየፈጸሙ እንደሆነ ራሳቸውን ይገመግማሉ	• 6ቱ ቃላተ ወንጌል	6ቱ ቃላተ ወንጌልን በመዘርዘር ለተማሪዎቹ ይንገሯቸው። ቀጥሎም እያንዳንዱ ተማሪ የሚከተለውን ጥያቄ መልስ በማስታወሻ ደብሩ ላይ እንዲጽፉ ያድርጉ። • በእናንተ አስተያየት ከተዘረዘሩት ትዕዛዛት ውስጥ ከባድ ነው የሚትሉት የትኛውን ነው? ለምን? የተወሰኑ ተማርዎችን በማስነሳት የጻፉትን እንዲያነቡ ካደረጉ በኋላ እያንዳንዱን ቃላተ ወንጌል ተራበተራ ለተማሪዎቹ ያስረዷቸው። ከተለመደው ትርጉም ባሻገር ከወቅቱና ከተማሪዎቹ ሕይወት ጋር በማገናኘት ያመሳጥሩት። በመጨረሻም ተማሪዎቹ ከሕግጋቱ አንጻር ሕይወታቸውን እንዲገመግሙና እንዲያስተካክሉ በማበረታታት ትምህረቱን ያጠቃልሉ።
• አንቀጸ ብፁአንን ይዘረዝራሉ • የእያንዳንነዱን አንቀጽ ምሥጢር ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ ያብራራሉ • ከአንቀጸ ብፁአን አንጻር ሕይወታቸውን ይገመግማሉ	አንቀጸ ብፁአን	አንቀጸ ብፁአንን ለማስተማር በማቴ 5፤12 ከተፈው ጋር ተቀራራቢ ሕይወት ያለውን የአንድ ቅዱስ አባት ታሪክ ከቅዱሳት መጻሕፍት ፈልገው በጽሑፍ አዘጋጅተው (ቢቻል በተማሪዎች ቁጥር አባዝተው) ይምጡ። አንቀጸ ብፁአንን ካነበቡላቸው በኋላ ተማሪዎችን በምድብ ከከፈሉ በኋላ በአንቀጸ ብፁአን ላይ ከተዘረዘሩት 9 ነገሮች አንጻር የቅዱሱን ታሪክ በመገምገም የትኞቹን እንደፈጸመ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ያድርጉ። የሁለቱን ምድብ ከሰሙ በኋላ የተለየ አስተያየት ላላቸው ምድቦች ብቻ እድል በመስጠጥ የእያንዳንዱን ምሥጢር ተራ በተራ ያብራሩላቸው። በተለይ "*የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፥ መፅናናትን ያገኛሉና።*" የሚለውን አንቀጽ ሲያብራሩ ከማቴ 25፤ 31-46 ጋር በማገናዘብ ያስተምሯቸው። በመጨረሻም ተማሪዎቹ ከንቀጸ ብፁአን አንጻር ሕይመታቸውን እንዲገመግሙ በማበረታታት ትምህርቱን ያጠቃልሉ።
• የመንፈስና የሥጋ ፍሬዎችን ይለያሉ። • የመንፈስ ፍሬዎችን ለማፍራት	የመንፈስ ፍሬዎች	ይህን ክፍል በሚከተለው ጥያቄ መጀመር ይችላሉ። • የመንፈስ ፍሬ ስንል ምን ማለታች ነው? የሥጋ ፍሬስ? የተወሰኑ ተማሪዎችን መልስ ካደመጡ በኋላ የሁለቱን ትርጉም በሚገባ ያስረዷቸው።

ይነሳሳሉ፡፡		በመቀጠልም ገላ 5፤ 19 ጀምሮ ያሉትን የመንፈስና የሥጋ ፍሬዎችን ይዘርዝሩላቸው፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎቹ ከነዚህ ፍሬዎች አንጻር ሕይወታቸውን እንዲመረምሩና ከሥጋ ፍሬዎች ተቆጥበው የመንፈስ ፍሬዎችን ለማፍራት እንዲነሳሱ በማበረታታት ያጠቃልሉ፡፡

ምዕራፍ ሦስት፡- የክርስትያናዊ ተጋድሎ መንገዶች /6 ሰዓት/

ከተማሪዎቹ የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት

- የክርስቲያናዊ ተጋድሎን ምንነትና አስፈላጊነት ይገነዘባሉ
- የክርስቲያናዊ ሕይወት መሠረታዊያንን በመገንዘብ የሕይወታቸው መርሕ ለማድረግ ይነሳሳሉ
- የጾም፤ የጸሎትና የስግደትን ምንነትና ጥቅም በመረዳት የህወታቸው መርህ ለማድረግ ይዘጋጃሉ

የሚጠበቅ ብቃት	ይዘት	የመማር ማስተማር ክንውን
• የኃጢአትን ምንነትና ውጤት ያብራራሉ • የክርስቲያናዊ ተጋድሎን ምነናትና አስፈላጊነት ይገልጻሉ • በክርስቲያናዊ ተጋድሎ የምገኘውን ዋጋ ይናፍቃሉ	3.1 ክርስቲያናዊ ተጋድሎ • የኃጢአት ምንነትና ውጤት • የተጋድሎ ምንነትና ውጤቱ	ይህን ክፍለ ትምህርት በሚከተለው ጥያቄዎች ይጀምሩ • ሰው ኃጢአት ሰራ ወይንም እራሳችሁ ኃጢአት ሰራን የምትሉት መቼ ነው? ኃጢአት መሆኑ በምን ይታወቃል? ተማሪዎቹ በቡድን ሁነው ወይንም ጎን ለጎን የተቀመጡ ሦስት ተማሪዎች ተወያይተው መልሳቸውን በማስታወሻ ደብተር እንዲጽፉና የተወሰኑት ተነስተው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡ በመቀጠልም ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ የኃጢአትን ምንነትና ውጤት ያስረዷቸው፡፡ ለሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት ይስጡ ኃጢአትንና የኃጢአት መንገዶችን ለይተው ያብራሩላቸው • ሰው ኃጢአትን መተው ያለበት ይጎዳኛል ብሎ እንጂ ፈርቶ መሆን እንደለሌበት ያስገንዝቡ • ሁሌ ሰውን ኃጢአት እንዲሰራ የሚገፋፋው ሴይጣን ብቻ እንደ ሆነ ማሰብ ተገቢ እንዳልሆነ ያስረዱ በመጨረሻም "ምኞት ጸንሳ ኃጢአትን ትወልዳለት፤ ኃጢአትም ሞትን ትወልዳለች" የሚለውን የሚለውን ጥቅስ በማብራራት ማጠቃለል ይችላሉ፡፡ የተጋድሎን ምንነትና ውጤት በተመለከተ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ 1. መንፈሳዊ ተጋድሎ ምንድን ነው?

		2. የክርስትና ሕይወት የተጋድሎ ሕይወት የሆነው ለምንድን ነው? 3. ሰው የሚጋደለው ከምን ጋር ነው? 4. ያለ ተጋድሎ ክርስቲያን መሆን ይቻላል? ተማሪዎቹ ጥያቄዎቹ ላይ ከተወያዩ በኋላ በአእያንዳንዱ ጥያቄ ተራ በተራ የተወሰኑ ቡድኖችን መልስ ከተናገሩ በኋላ አስፈላጊውን ማስተካከያና ማብራሪያ ይስጡ። በመቀጠልም ተጋድሎ እንደ ወቅቱ፤ ቦታውና የክርስትና ጥንካሬ እንደሚለያይ በማስረዳትና ከዘመኑ ትውልድ /ከተማሪዎች/ የሚጠበቀው ተጋድሎ ምን እንደሆነ በማብራራት ማጠቃለል ይቻላል።
• የክርስትያናዊ ሕይወት መሠረታዊያንን በቅዱሳት መጻሕፍት አስረጅነት ይተነትናሉ • ከክርስትያናዊ ሕይወት መሠረታዊያን አንጻር ሕይወታቸው ገምግመው ራሳቸውን ለማስተካከል ይወስናሉ።	3.2 የክርስትያናዊ ሕይወት መሠረታዊያን • ፍቅር • ይቅርታ • ትዕግስት • ትሕትና • ቅንነት	ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል ለእያንዳዱ ቡድን ከተዘረዘሩት የክርስትና ሕይወት መሠረታዊያን አንድ በመስጠት አብነት የሚሆን የአንድ አባት/እማት/ ታሪክ ጠይቀው ወይንም ከቅዱሳት መጻሕፍት አንብበው እንዲመጡና ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ያድረጉ። ተማሪዎቹ በቂ ጊዜ እንዲኖራቸው አስቀድሞ መስጠት ያስፈልጋል። በመቀጠልም እያዳንዱ ርዕስ ላይ ተማሪዎቹ ካቀረቡ በኋላ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት ያደረገ ማብራርያ ይስጡ፤ ተማሪዎች ከክርስትያናዊ ሕይወት መሠረታዊያን አንጻር ሕይወታቸው ገምግመው ራሳቸውን እንዲያስተካክሉ ያበረታቷቸው።
• የክርስቲያናዊ ጾምን ምንነት ያብራራሉ • የጾምን ጥቅም ይዘረዝራሉ • ለመጾም ይወስናሉ • ከክርስቲያናዊ ጾም ጠባያት	3.3 ጾም • የክርስቲያናዊ ጾም ምንነት • የጸም አጀማመር • የጾም አይነቶች	በዚህ ክፍለ ትምህርት ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ የጾምን ትርጉምና አጀማመር፤ የጾም ዓይነቶችን እና የክርስቲያናዊ ጾም ጠባያትን ያስረዷቸው። ለምከተሉት ጉዳች ትኣኩረት ማስጠት ያስፈልጋል። • ጾም ከእህልና ውኃ መከልከል ባለፈ ሁሉም የስሜት ሕዋሳት (ጆሮ፤ ዓይን፤ እጅ፤ እግር፤ ወዘተ/ መጾም እንዳለባቸው

አንጻር የጾም ሕይወታቸውን ይመረምራሉ	• የክርስቲያናዊ ጾም ጠባያት	• ጾምን እንደ ሸክም ሳያዩ በፍቅር መጾም እንዳለባቸው፤ በተለይ በግቢ ውስጥ እያንዳንዱ ተማሪ ሌላውን ሰው እያየ ሳይሆን እንደ አቅሙ መጾም እንዳለበትና በሂደት በልምምድ ራሱን ማሳደግ እንዳለበት • ሰው ሲታመም፤ በሀኪም ትዕዛዝ መድኃኒት የሚስድ ከሆነ፤ የጉልበት ሥራ የሚሰራ ሰው፤ ወዘተ. እንዴት መጾም እንዳለበት /እነዚህ ነገሮች ሲገጥሟቸው ከንስሃ አባት ጋር መነጋገር እንደሚገባ/ በመቀጠል ተማሪዎቹ ጥያቄ እንዲጠይቁ እድል ይስጧቸው፡፡ በመጨረሻም ከክርስቲያናዊ ጾም ጠባያት አንጻር ሕይወታቸውን እነዲገመግሙና በአግባቡ ለመጾም እንዲወስኑ ያበረታቷቸው፡፡
• የክርስቲያናዊ ጸሎትን ምንነት ያብራራሉ • የጸሎትን ጥቅም ይዘረዝራሉ • በተመስጦ ለመጸለይ ጥረት ያደርጋሉ • በጸሎት ለመበርታት ይወስናሉ	3.4 ጸሎት • የጸሎት ምንነት • የጸሎት ጥቅም • ሥርዓተ ጸሎት • የጸሎት ዓይነቶች • ተመስጦ	በዚህ ክፍለ ትምህርት ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ የጸሎትን ትርጉምና ጥቅም፤ የጸሎት አይነቶችን እና ሥርዓተ ጸሎትን ያስረዷቸው፡፡ በመቀጠልም ግልጽ ያልሆነ ሀሳብ ካለ እንዲጠይቁ እድል ይስጧቸው በመቀጠልም ተማሪዎቹ በቀጣዩ ጥያቄ ላይ በቡድን እንዲወያዩ ያድርጉ፡፡ • ደስ ብሏችሁ የምትጸልዩት መቼ ነው? • ተመስጦን እንዴት ማምጣት ይቻላል? ተማሪዎቹ የተወያዩበትን ካቀረቡና ዉይይት ከተደረገበት በኋላ ተመጦን ለማምጣት የሚነገሮችን በዝርዝር ያስረዷቸው፡፡ የሚከተሉትን እንደመነሻ መጠቀም ይቻላል • በዝግጅት • ሂሊናን ከሚበታትኑ ነገሮች ነጻ መሆን • በስግደት መጀመር • መለማመድ • ስለ ተመስጦ ሳይጨነቁ መጸለይ፤ ወዘተ

		በመጨረሻም ስለ ጸሎት ከተሰጣቸው ትምህርት አንጻር ሕይወታቸውን እነዲገመግሙና እንዲያስተካክሉ በማበረታታት ያጠቃልሉ፡፡
• የስግደትን ምንነት ያብራራሉ • የስግደትን ዓነቶች ይለያሉ • የስግደትን ጥቅም ይዘረዝራሉ • ስግደታቸውን ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን የተከተለ ለማድረግ ይነሳሳሉ	3.5 ስግደት • የስግደት ትርጉም • የስግደት ዓይነቶች • የስግደት ጥቅም • ሥርዓተ ስግደት	በዚህ ክፍለ ትምህርት ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ የስግደትን ትርጉም፤ የስግደት ዓይነቶን ፤ የስግደት ዓይነቶችን እና የስግደት ሥርዓትን ያስረዷቸው፡፡ በመቀጠል ተማሪዎቹ ጥያቄ እንዲጠይቁ እድል ይስጧቸው፡፡ በመጨረሻም ከተሰጣቸው ትምህርት አንጻር ሕይወታቸውን እነዲገመግሙ በማበረታታት ያተቃልሉ

ምዕራፍ አራት፡- መባእ እና ምጽዋት /1 ሰዓት/

ከተማሪዎች የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት

- የመባእ እና የምጽዋትን ምንነትና ጥቅም ይገነዘባሉ
- የማባእ እና የምጽዋትን አፈጻጸም ያስረዳሉ
- መባቸውን እና ምጽዋታቸውን በሥርዓተ ቤተክርስቲያን ለማድረግ ይወስናሉ፡፡

የሚጠበቅ ብቃት	ይዘት	የመማር ማስተማር ክንውን
• የመባእን ምንነት ያስረዳሉ • መበእ በመስጠት የሚገኘውን ጥቅም ይዘረዝራሉ • አስራት፤ በኩራትና ቀዳሚያት የሚሉ ጽንሰ ሐሳቦች ያብራራሉ • የምጽዋትን ምንነት ያስረዳሉ • የምጽዋትን ጥቅም ይዘረዝራሉ • የሚፈጽሙትን መባእ እና ምጽዋት ከሥርዓተ ቤተክርስቲያን አንጻር ይገመግማሉ	4.1 መባእ • የመባእ ምንነትና ጥቅም • አሥራት፤ በኩራት፤ ቀዳሚያት • መባእ በሀዲስ ኪዳን 4.2 ምጽዋት • የምጽዋት ምንነትና ጥቅም • ሥርዓተ ምጽዋት	በዚህ ክፍለ ትምህርት በይዘት ሥር የተዘረዘሩትን ይዘቶች ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ ያስረዷቸው፡፡ በመቀጠልም የሚከተለውን ጥያቄ በማንሳት ተማሪዎቹ በቡድን እንዲወያዩበት ያድርጉ • በመባእ እና ምጽዋት አፈጻጸም ላይ ያሉት ተግዳሮቶች ን ዘርዝሩ • ለእያንዳዱ ተግዳሮች የመፍትሔ ሐሳቦች አቅርቡ ተማሪዎች ካቀረቡ/ከተናገሩ/ በኃላ አስፈላጊውን ማስተካከያ ከሰጡ በኃላ ከሥርዓተ ቤተክርስቲያን አንጻር የራሳቸውን ሕይወት እንዲገመግሙ በማበረታታት ትምህርቱን ያጠቃልሉ፡፡

ምእራፍ አምስት፡- ክርስቲያናዊ የሕይወት መንገዶች

ከተማሪዎች የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት

- የክርስቲያናዊ ሕይወት መንገዶችን ምንነትና ታሪክ ይረዳሉ
- በክርስቲያናዊ ሕይወት መንገዶች መንገዝ የሚያስገኘውን ክብር ይገነዘባሉ
- በክርስቲያናዊ የሕይወት መንገዶች በአንዱ ለመንገዝ ራሳቸውን ያዘጋጃሉ

የሚጠበቅ ብቃት	ይዘት	የመማር ማስተማር ክንውን
• የድንግልና እና የጋብቻን ሕይወት ምንነት ያብራራሉ	5.1 መግቢያ • ስለ ድንግልና እና ጋብቻ ሕይወት	መምህሩ የክፍለ ትምህርቱን ዓላማ በመግለጽ ትምህርቱን ይጀምራል። በመቀጠልም በክርስትና ሁለት የሕይወት መስመሮች (ድንግልና እና ጋብቻ) እንዳሉ በመጥቀስ የሁለቱን አጠቃላይ ትርጉም ያብራራ። በመጨረሻም ወደ ቀጣዩ ክፍል ከመግባቱ በፊት ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁ እድል ከሰጠ በኋላ ትምህርቱን ያጠቃልላል።
• ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ የድንግልናን ሕይወት ምንነት ያስረዳሉ • የምንኩስና፤ የብህትውና እና ገዳማዊ ሕይወትን አንድነትና ልዩነት ያብራራሉ • የምንኩስና፤ የብህትውና እና ገዳማዊ ሕይወትን ታሪክና ክብር ይተርካሉ • የምንኩስና፤ የብህትውና እና ገዳማዊ ሕይወት አኗኗርና	5.2 ክርስቲያናዊ አኗኗር በድንግልና • የድንግልና ሕይወት ምንነትና ታሪክ • የድንግልና ሕይወት ጥቅምና ክብር • ምንኩስና ፤ ብሕትውና እና ገዳማዊ ሕይወት	ይህን ትምህርት የድንግልና ሕይወትን ትርጉም በማስታወስ መጀመር ይቻላል። በመቀጠልም የአባቶችን ሕይወት መሠረት በማድረግ (ነቢዩ ኤልያስ፤ መጥምቁ ዮሐንስ፤ ወዘተ. . .) የድንግልናን ሕይወት ታሪክና የሚያስገኘውን ክብር ያስገንዝቧቸው። በመቀጠልም ተማሪዎችን በቡድን በመክፈል *የድንግልና፤ የምንኩስና እና የብህትውናን ልዩነትና አንድነት* ተወያይተው እንድጽፉና እንዲያርቡ ያድርጓቸው። በመቀጠልም ከተማሪዎቹ መልስ በመነሳት የሦስቱን አንድነትና ልዩነት፤ ታሪክ እና ክብር ቅዱሳት መጻሕፍትና የአባቶችን ሕይወት በማንሳት በሚገባ ያስረዷቸው። በማስቀጠል የሚከተለውን ጥያቄ ጠይቀው ያወያዩዋቸው *"አንድ ሰው የሕይወት መስመሩን እስኪወስን ድረስ ድንግልናውን ጠብቆ ለመኖር ያሉት ተግዳሮቶችን /challanges/ ዘርዝሩ"* ።

ተጋድሎ ያደንቃሉ፡፡ • የሕይወት መስመራቸውን እስኪለዩ ድረስ በድንግልና ፀንተው ለመኖር ይወስናሉ	(ምንነቱ፤ ታሪኩና ጥቅሙ)	ተማሪዎቹ ያነሷቸውን ተግዳሮቶች በጽሑፍ ከያዙ በኋላ ለእያንዳንዱ መፍትሔ የሚሉትን እንድናገሩ ያድርጉ፡፡ በመጨረሻም የሕይወት መስመራቸውን እስኪለዩ ድረስ ንጽህናቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ አጽንኦት በመስጠት ያጠቃልሉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በግል/በጋራ በመሆን ሚከተሉት ተግባራት እንድያከናውኑ ያበረታቷቸው፡፡ • የአባቶችን ሕይወት የሚያሳዩ ፊልሞችን እንዲመለከቱ • በቅዱሳን አባቶች ሕይወት ዙሪያ የተጻፉ መጻሕፍት እንዲያነቡ • በግል ወይም በህብረት ወደ ገዳማት ጉዞ በማድረግ የአባቶችን አኗኗር እንዲመለከቱ
5.3 ክርስትያናዊ አኗኗር በጋብቻ		
• የጋብቻን ምንነትና አስፈላጊነት ያስረዳሉ	5.3.1 መግቢያ	የዚህን ክፍለ ትምህርት የርዕሱን ዝርዝር አላማዎች በማስረዳት ይጀምሩ፡፡ በመጠልም ቅዱሳት መጻሕፍን መሠረት በማድረግ ሦስቱን የጋብቻ ዓላማዎች (ዘር ለመተካት፤ ለመረዳዳት እና ከፈተና ለመጠበቅ) በሚገባ ያስረዷቸው፡፡
• ጾታዊ ቅርርቦሻቸውን በክርስቲያናዊ ሥርዓት ይመራሉ	5.3.1 ጾታዊ ቅርርቦሽ	ተማሪዎቹን በቡድን በመክፈል (ወንዶችን እና ሴቶቸን ለብቻ) የሚከተለው ጥያቄ ላይ እነዲወያዩ ያድርጉ • *የግቢ ጉባኤ ሴቶችና ወንዶች ቅርርብ ምን መምሰል አለበት?* በመቀጠል ሴቶቹ የተወያዩበትን እንዲያቀርቡ በማድረግ ወንዶቹ አስተያየት እንዲሰጡበት ያድርጉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ወንዶቹ እንዲያቀርቡ ያድርጉና ሴቶቹ አስተያየት እንዲሰጡ ያድርጉና ያጠቃልሉ፡፡ በማጠቃለያዎ ላይ የሚከተሉ ነጥቦችን ማጽናት ያስፈልጋል • ነጻነትን በሚነፍግ (በሚያሸማቅቅ መልኩ) መሆን የለበትም • ወደ ፈተና እንዳይገቡ ቦታ ግዜና ሁኔታዎችን መለየት ያስፈልጋል • ለቅርርቦሽ ስሜታዊ ብስለት /emotional maturity/ እንዲኖራቸው • ከሁሉም ጋር ተመጣጣኝ ቅርርቦሽ ማድረግ /መቀቀያየር/

• በጋብቻ ሕይወት በመተጫጨት በፊት የሚደረገውን ዝግጅት ይተነትናሉ	5.3.3 ከመተጫጨት በፊት ስላለው ሕይወት/ዝግጅት/	ተማሪዎቹን የሚከተለውን ይያቁ በመጠየቅ ያወያየአቸው፡፡ • *አንድ ሰው የትዳር ጓደኛ በማጨቱ በፊት ማሟላት ያለባቸው ነገሮችን ዘርዝሩ፡፡* ተማሪዎቹ የሚዘረዝሯቸውን ነገሮች በማስታሰሻ ከያዙ በኋላ ትክክለኛ የሆኑትንና ያልሆኑትን በመለየት ለምን ትክክል እንዳልሆኑ ያስረዷቸው፡፡ መሟላት ያለባቸው ነገሮችን በተመለከተ የሚከተሉት አራት ነገሮች በአግባቡ ለተማሪዎቹ ማስጨበጥ ያስፈልጋል፡፡ ▪ መንፈሳዊ ብስለት ▪ አዕምሮአዊ ብስለት ▪ አካላዊ ብቃት ▪ ኢኮኖሚያዊ ብቃት
• ክርስቲያናዊ የትዳር ጓደኛ መምረጫ መስፈርቶችን ይለያሉ • የመተጫጨትን ዓላማ ያስረዳሉ • የጾታዊ ፍቅር መገለጫዎችን ይገልጻሉ • በእጮኝነት ሕይወት ሊኖር የሚገባውን ሥርዓት ይገመግማሉ	5.3.4 *መተጫጨት* • የመተጫጨት ዓለማ • ጾታዊ ፍቅር • የትዳር ጓደኛ ምርጫ • የእጮኝነት ሕይወት	ይህን ክፍለ ትምህርት ሲጀምሩ የሚከተለውን ጥያቄ ጠይቀው ማወያየት ይችላሉ፡፡ • አንድ ሰው ለእጮኝነት ቢጠይቅሽ/ህ ምን ይሰማሻል/ሀል? የተማሪዎቹን ሀሳብ ከሰሙ በኃላ አንድ ሰው ለትዳር ጓደኛነት ሲጠየቅ እንዴት ማስተናገድ እንዳለበት የቤተክርስቲያኒቱን አስተምህሮ መሠረት በማድረግ ያስረዷቸው፡፡ በመቀጠልም የመተጫጨትን ዓላማ ያስገንዝቧቸው፡፡ የትዳር ጓደኛ መምረጫ መስፈርቶችን ሲያስተምሩ በሚለተው ጥያቄ ላይ ታሪዎቹን በቡድን ይወያዩ፡፡ • የትዳር ጓደኛ መምረጫ መስፈርቶችን ዘርዝሩ በመቀጠልም ከተዘረዘሩት መስፈርቶች ተገቢ የሆኑትንና ያልሆኑትን በመለየት ያስረዷቸው፡፡ ቅድሚያ ሊሰጣቸው ከሚገቡ መስፈርቶች ውስጥ ሃይማኖት (ክምግባር የተስማማ እምነት)፤ የእድሜ መቀራረብ፤ የጠባይ መግባባት ፤ወዘተ ትኩረጥ ሰጥተው ያስረዷቸው፡፡

		ይህን ክፍለ ትምህርት ከመጀመር ቀደም ብሎ ባለው ሳምንት ለተማሪዎች የሚከተለውን ግብረ ቤት ሰርተው እንዲመጡ ይንገሯቸው። የቤት ሥራው በግል ወይንም በቡድን ሊሰጣቸው ይችላል። • *ሁለት እጮኛሞች የእጮንነት ግዜያቸውን እንዴት ማሳለፍ አለባቸው?* ተማሪዎቹ የቤት ሥራቸውን እንዲያቀርቡ ዕድል ይስጧቸው (ተማሪው ብዙ ከሆነ የተወሰኑት ብቻ እንዲያቀርቡ ማድረግ ይቻላል)። በማጠቃለያው በጮኝነት ግዜ በደንብ መግባባትና መተዋወቅን ከፈተና ከመጠበቅ ጋር በተጣጣመ መልኩ ማሳለፍ እንደሚገባ እና የእጮኝነት ግዜ የመጠናኛ ግዜ እንደ መሆኑ ፈቃደ እግዚአብሔር ካልሆነ ሊቀር እንደሚችል ማሳወቅ ያስፈልጋል። ታማሪዎቹ ጥያቄ ካላቸው እንዲጠይቁ እድል ይስጧቸው።
• የክርስቲያናዊ ጋብቻ መገለጫዎችን ይለያሉ	5.3.4 ክርስቲያናዊ ጋብቻ	ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ አንድን ጋብቻ ትክክለኛ/ክርስቲያናዊ ጋብቻ/ ሊያሰኙ የሚችሉ መገለጫዎችን ያብራሩላቸው። ተማሪዎቹ ጥያቄ ካላቸው እድል ይስጧቸው
• ሠርግ በክርስተያናዊ ጋብቻ ያለውን ቦታ ይገመግማሉ	5.3.5 ሠርግ	በሰርግ አስፈላጊነትና የትክክለኛው የቤተክርስቲያን ሰርግ ላይ ሀሳብ እንዲሰጡ ለተወሰኑ ተማሪዎች እድል ይስጡ። በመቀጠልም ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ የትክክለኛውን ሰርግ መገለጫዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት ማድረግ ገለጻ በማድረግ ማጠቃለል ይቻላል።
• ክርስቲያናዊ የቤተሰብ መገለጫዎችን ይተነትናሉ	5.3.6ክርስቲያናዊ የቤተሰብ አስተዳደር	ይህን ትምህርት በሚከተለው ጥያቄ ይጀምሩ • *ሴቶች ጥሩ ባል የምትሉት ምን ዓይነት ነው?* • *ወንዶች ጥሩ ሚስት የሚትሉት ምን አይነት ነች?* በመጀመሪያ ሴቶችን ያወያዩና በሴቶቹ ሀሳብ ላይ ወንዶች አስተያየት እንዲሰጡ ያድርጉ። በተመሳሳይ መልኩ በወንዶች ሀሳብ ላይ ሴቶቹ ሀሳብ ከሰጡ በኋላ

		አስፈላጊውን ማብራሪያ በመስጠት ያጠቃልሉ፡፡
• ክርስቲያኖች ደስታና ሀዘንን እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው ያብራራሉ	5.3.7 ደስታና ሀዘን	አንድ የክርስቲያን ቤተሰብ ደስታና ሀዘን ሲገጥመው እንዴት ማሳለፍ እንዳለባቸው የተወሰኑ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡ በጥያቄ መልክ ያቅርቡላቸውና በመቀጠልም ከቤተክርስቲያኒቱን አስተምህሮና ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ ያብራሩላቸው፡፡

የሚጠበቅ ብቃት/ /	ይዘት / /	የመማር ማስተማር ክንውን / / እና ዘዴዎች /ግብዓቶች

በሠርግ መካከል ያለውን ልዩነትና አንድነት ያስረዳሉ። • የክርስቲያናዊ ቤተሰብ አስተዳደር ምን እንደሚመስል የብራራሉ። • ክርስቲያናዊ ቤተሰብ አስተዳደር ምን እንደሚመስል ያብራራሉ። • ክርስቲያኖች ደስታና ሐዘንን የሚያስተናገዱበትን ሁኔታ ይናገራሉ። • ክርስቲያናዊውን ጋብቻ ከሌላው ጋብቻ ጋር ያነጻጽራሉ።	5.3.5. የክርስቲያናዊ ቤተሰብ አስተዳደር 5.3.6. ደስታና ሐዘን	• ክርስቲያናዊ የቤተስ አስተዳደር ምን መምሰል አለበት? • ክርስቲያኖች ደስታና ሐዘንን የሚያስተናግዱበት መንገድ /ሁኔታ/ ምንድነው? እነዚህን ጥያቄዎች ከላይ ባየናቸው ጥያቄዎች አቀራረብ መሠረት ወይም በቅደም ተከተል ለውይይት ክፍት ያድርጉ፤ ማለትም በላይኛው አጠቃላይ ውይይት ከሆነ ያሁኑን በቡድን በማድረግ ወይም በግልባጩ በማመቻቸት የመማር ማስተማር ዘዴውን ማራኪ በማድረግ የተማሪዎችን ሱታፌ ከፍ ማድረግ ይችላሉ። ለዚህ ተግባር 1 ሰዓት ይጠቀሙ በቀረው 1 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ተማሪዎቹ ያቀረቡትን ምላሽ መሠረት በማድረግ እያስተካከሉና እያጎሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችንና ታሪኮችን እማኝ እያደረጉ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ይስጡ። በዚህም ረገድ ከክርስትና የወጡ ልምዶችን የጋብቻና የሠርግ አፈጻጸሞችንና ልቅ የሆነውንና ከመጠን በላይ ቁጥጥር በዝቶ የድብብቆሽ ሕይወት የሚያነግሰውን የቤተሰብ አስተዳደር እንዲሁም ደስታን በተለይም ሐዘንን ኢ ክርስቲያናዊ በሆነ መንገድ የሚገለጥበትን ሁኔታ በማብራራት ተማሪዎቹ ሕገወጥ ድርጊቶችን እየተጸየፉ ወደ ትክክለኛው መስመር እንዲገቡ ለማድረግ ያስችላል የሚሉትን ሁሉ ያድርጉ። ከዚሁ ከአንዱ ሰዓት የሚበቃዎትን ያህል ደቂቃዎች አስተርፈው ዋና ዋናዎቹን ሓሳቦች በመድገም ወይም ተማሪዎችን መሠረታዊ ጥያቄዎች በመጠየቅ አጠቃለው ወደ ሚቀጥለው ርእሰ ትምህርት /ምዕራፍ/ ይሸጋገሩ።

ምዕራፍ ስድስት፡ የክርስቲያኖች የሕብረት ኑሮ / 3 ሰዓት/

ከተማሪዎች የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት፡ ተማሪዎች ይህነ ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኋላ

- **ስለ ክርስቲያኖች የሕብረት ነሮ አጀማመርና አሁን ካለው የቤተክርስትያን ትውፊት ጋር ያለውን ዝምድና ይገነዘባሉ**
- **የሰንበቴ፣ የጽዋ ማኅበር፣ የዝክርና የእንግዳ መቀበል አጀማመር፣ አፈጻጸም ፣ ልዩነትና አስፈላጊነት ምን ምን እንደሆነ ይረዳሉ፡፡**

የሚጠበቅ ብቃት	ይዘት	የመማር ማስተማር ክንውን
• በዘመነ ሐዋርያትና በጥንቷ ቤተክርስቲያን የነበረውን የክርስቲያኖች የሕብረት አኗኗር ያብራራሉ	6.1. የክርቲያኖች የሕብረት ኑሮ በዘመነ ሐዋርያትና በጥንቷ ቤተክርስቲያን	ይህ ትምህርት የሚያተኩረው ክርስትያኖች እርስ በራሳቸው ያላቸውን የአንድነት ሕይወት ላይ ስለሆነ ከተማሪዎች አንጻርም ከሎሎች ጋር ያለ ግንኙነትን ሳይሆን ይህንኑ ብቻ ማዕከል በማድረግ ትምህርቱን ማቅረብ ይገባል፡፡ስለዚህም ይህንን ክፍለ ትምህርት ሲጀምሩ ከተማሪዎቹ መካከል አንድ ሰው ጋብዘው በሐዋ. 4 ላይ ያለውን የሐዋርያት የአንድነት ኑሮ እንዲያነብ ያድርጉት/ጓት፡፡ ከዚያም የተነበበውን የሐዋርያት ኑሮ በመጠኑ ካብራሩላቸው በሁዋላ(ያላቸውን ሁሉ በአንድነት ማድረጋቸው፤አንድ ልብ አንድ ሀሳብ መሆናቸው፤በጎበረት መጸለያቸው ወዘተ) አሁን በግቢ ጉባኤ ውስጥ ተማሪዎች ከሚኖሩት የአንድነት ኑሮ ጋር ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድንው? የሚለውን ጥያቄ ይጠይቁዋቸው፡፡ እርሱን መልሰው ሲያበቁ ዛሬ ይህንን ኑሮ ለመኖር እንቅፋት የሆነው ነገር ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ ያንሱላቸውና እርስ በራሳቸው እንዲወያዩ ጊዜ ይስጡዋቸው፡፡ ከዚያም ትምህርቱን ሲያጠቃልሉ ክርስትና ራሱ በምድር ያለን ክርስትያኖ ከሰማያውያን መላዕክት ጋር ለክርስትያኖች የጎበረት ኑሮ አስፈላጊ መሆኑን በማስረገጥ ለዚህ ደግሞ ትዕግስት፤ ፍቅር፤ መደማመጥ እና ጠንካራ እምነት እንደሚያስፈልግ ይግለጹላቸው፡፡ ይህንን የአንድነት ኑሮ ላለመኖር ፈተና የሆኑ ጉዳዩችን ከግለሰቦች አመለካከትና ፍልስፍና(ግቢ ጉባኤ አንድነት ለምን ያስፈልጋል ከሚሉ ወዘተ...) እና

		ሌሎች ጉዳዩች ጋር አንስቶ ማወያየት ወይም ታሪኮችን አንስቶ ማዳበር የበለጠ ትምህርቱን ያጠናክረዋል። በዚህ ክፍለ ትምህርት መጨረሻ ለሚቀጥለወ ሳምንት ተማሪዎቹ ሠርተው የሚመጡትን የቤት ሥራ ይስጡዋቸው። በዚህ ወቅት ተማሪዎቹ በመደበኛ ትምህርታቸው ላይም የቤት ሥራዎች እና ውይይት ያሰለቻቸው ሊሆን ስለሚችል የቤት ሥራውን ከመስጠት በፊት ለተማሪዎቹ ጥቂት ገለጻ በማድረግ እንዳይሰላቹና እንዳይተውት ቢያደርጉ መልካም ነው።
• በዛሬይቱ ቤተክርስቲያን ያለውን ሐዋርያዊ የሕብረት ኑሮ ያብራራሉ • የሰንበቴ፣ የጽዋ ማኅበር፣ እንግዳ አቀባበልና ዝክር አፈጻጸሞችንና ልዩነቶቻቸውን ያስረዳሉ • የሰንበቴ፣ የጽዋ ማኅበር፣ እንግዳ አቀባበልና ዝክር ምንነትና ጥቅም በመረዳት በነዚህ ለመሳተፍ ይወስናሉ፤የያዙትንም ያጠራክራሉ • ክርስቲያናዊውን የሕብረት ኑሮ በጊዜያችን በዓለም ላይ ከሰፈነው ግለኝነት አንጻር	6.2. ሐዋርያት የሕብረት ኑሮ በዛሬይቱ ቤተክርስቲያን • ሰንበቴ • የጽዋ ማኅበራት • እንግዳ መቀበል • ዝክር	ይህንን ክፍለ ትምህርት ከመጀመር ቀደም ብሎ ባለው ሳምንት ለተማሪዎቹ የሚከተለውን ግብረ ቤት ሠርተወ እንዲመጡ ይንገሩዋቸው። የቤት ሥራው በቡድን ሊሰጣቸው ይችላል። *ባላችሁበት አጥቢያ ውስጥ ያሉ የጽዋ ማህበራትን በመዘርዘር ሥርዓታቸውን አስረዱ። ባላችሁበት አጥቢያ ሰንበቱ አለ ወይስ የለም?* ትምህርቱን ሲጀምሩ የዕለቱን ትምህርት ዓላማ ካስተዋወቁዋቸው በሁዋላ የሰጡዋቸውን የቤት ሥራ እንዲያቀርቡ ለተማሪዎቹ እድል ይስጡዋቸው። ከዚያም በቅዱስ መጽሐፍ 1ኛ ቆሮ 10-11 ላይ የተጠቀሰውን አንብበው በአጥቢያቸወ ያዩት ሥርዓት በቅዱስ መጽሐፍ ከተጠቀሰው ጋር ያለዋን ልዩነት እንዲያብራሩ ጊዜ ይስጡዋቸው። ተማሪዎች ጥያቄ እንዲጠይቁ ያድርጉዋቸው። ይህንን ከፈጸሙ በሁዋላ እንግዳ መቀበልን ጌታችን በቅዱስ ወንጌል ማቴ 25 የተናገረውንና ከቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት ዕብ 13:5 ላይ ያላውን ሌሎችም የቅዱሳንን ታሪክና ከመጻሕፍት ያገኙትን በመጥቀስ ያብራሩላቸው። ከዚህም በሁዋላ የሚከተለውን ታሪክ ወይም መሰል ታሪክ ይንገሩዋቸው። *አንድ ወጣት አግቢ ጉባኤ ተመርቆ በአንድ አጥቢያ በሰንበት ትምህርት ቤትና በሰበካ ጉባኤ ያገለግላል። በመሥሪያ ቤቱም በሰፈሪም የተወደደ ሰው አክባሪ ወጣት ነው። አንድ ቀን ሥራ አምሽቶ ሦስት ሰዓት ላይ ወደ ቤቱ ሲመጣ ቤቱ አካባቢ አንድ የተቸገረ ማደሪያ ያጣ ጎልማሳ ያገኝና ቤት የእግዚአብሔር ነው ብሎ በማዘን ወደቤቱ ይወስደዋል። እግሩን አጥቦ ራት አብልቶ መኝታውን ለቆ ያስተኛዋል። ሌሎት ችግረኛ የተባለዋ ሰው*

ይገመግማሉ።		*ተነስቶ ቤቱን ሲበረብር ይነቃል። ምን እንደተፈጠረ ለማየት ሲነሳ ችግረኛ የተባለው ሰው ድንገት ግንባሩን ይፈነክተውና ያገኘውን ነገር ሁሉ ወስዶ በሌሎት ይጠፋል። ወጣቱም እንደምንም የተፈነከተውን ግንባሩን አስሮ ሰልክ ጉዋደኞቹ ጋር ከደወለ በሁዋላ ይተርፋል። የተከራየቤት ቤት ሰፈርተኞች ይህንን ሲሰሙ በሌባ መዘረፉ ሳያሳዝናቸው ሌባ አስለመደብን ብለው ከሰፈራቸው እንዲወጣ አከራዩን አነሳሱበት። ወጣቱም ለጊዜው የደረሰበትን ችግር እንደምንም ቢቋቋምም በዘመናችን እንግዳ መቀበል የማይቻል ነው ሲል ሁለተኛ እንግዳ ላለመቀበል ወሰነ ለዚህ ወጣት ምን ትመክሩታላችሁ?* **ይህንን ውይይት ጽድቅን መሥራት መከራ ሊኖረው እንደሚችል ሆኖም ግን ሰው ጽድቅን ሲሰራ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበትና በጅምላ መደምደም እንደማያስፈልግ ነግረው ትምህረቱን ያጠቃሉ። ይህንን ከጨረሱ በሁዋላ ዝክር የሚለውን ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ አስፈላጊነቱንና ጥቅሙን ይግለጹላቸው። በመጨረሻም የሚከተለውን ጥያቄ ጠይቀው ያወያዩዋቸው።** • *ሰንበቴ፣ ዝክር ፣ የጽዋ ማኅበራትን መሳተፍ የኑሮ ዕቅድን ያዛባል፤ ለድኅነትም ያጋልጣል፤ የሚለውን አባባል በጋራ ተወያይበት።* **በአከራካሪ ነጥቦች ላይ ሓሳቦችን እንዲሰጡ ካደረጉ በኋላ በመጨረሻዎቹ 10 ደቂቃዎች የጥያቄዎቸን እና የክርክሩን ሐሳብ በአጭሩ ያጠቃሉ። በተለይም ሰንበቴ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ የጨረሰባትንን ያረፈባትን የብሉይ ኪዳን ሰንበት እንድትከበር እንዳዘዘ ሁሉ በአዲስ ተፈጥሮ የሰውን ልጅ ፈጥሮ ሥራውን የጨረሰባትን(ሞቶ ተሰቅሎ ከሙታን ተለይቶ የተነሳባትን) ዕለተ ሰንበትን ለማክበርና እርስዋንም በማሰብ ለዘላለማዊ ዕረፍት የሚሆን መልካም ሥራ ለመሥራት፤ በማኅበራዊ ሕይወት ለመረዳዳት ነዳያንን ለማሰብ የሚቋቋም በዕለተ ሰንበት ብቻ የሚሰበሰብ እንደሆን፤ ጽዋ ማኅበራትም ለቅዱሳን በተሰጠው አምላካዊ ቃል ኪዳን መሠረት የነሱን በረከት ለማግኘትና ፍለጋቸውነ ለመሳተፍ የሚጀመር ስብስብ እንደሆነና በሐዋርያት ዘመን ጀምሮ የነበረ መሆኑን፤ዝክርም**

		ለሙታን ዘመዶቻችን ወይም ቅዱሳንን ለማሰብ የሚደረግ ዝግጅት መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍትን ማስረጃ በማድረግ ማስገንዘብ ያስፈልጋል። እነዚህን ሲያደርግም ሰው አስቀድሞ በእምነት ሊያደርጋቸው፤ ሁለተኛ በደረጃውና በአቅሙ ሊፈጽማቸው የሚገባ መሆኑን ይግለጹላቸው።

ምዕራፍ ሰባት ፡ ክርስትና በማኅበራዊ ሕይወት /3 ሰዓት/

ከተማሪዎች የሚጠበቅ አጠቃላይ ውጤት፡ ይህን ምዕራፍ ከተማሩ በኋላ ተማሪዎች

- **ክርስቲያን በማኅበራዊ ሕይወቱ ምን መምሰል እንዳለበት ይገነዘባሉ**
- **ቁሳዊ ሀብትንና ሥራን ከክርስትና ጋር እንዴት አጣጥሞ መጓዝ እንደሚገባ ይረዳሉ**
- **ክርስትያን በዜግነቱ ብቻ ሳይሆን ሕዝብንና ሀገርን በመውደድ ሊያደርግ የሚገባውን ነገሮች ይገነዘባሉ፡፡**

የሚጠበቅ ብቃት/ /	**ይዘት**	**የመማር ማስተማር ክንውን / / እና ዘዴዎች /ግብዓቶች**
• **ከክርስቲያን የሚጠበቁ ሀገራዊና ማኅበራዊ አስተዋጽኦችን ይዘረዝራሉ** • **የሚጠበቅባቸውን ሀገራዊና ማኅበራዊ አስተዋጽኦ ለማበርከት ይነሳሳሉ**	7.1. **የክርስቲያን ሀገራዊ ማኅበራዊ አስተዋጽኦ**	**ይህንን ምዕራፍ ሲጀምሩ አጠቃላይ የምዕራፉን ዓላማ በማስተዋወቅ ቢጀምሩ ጥሩ ነው፡፡ ከዚያም የክርስትያናዊ ሥነ ምግባር መነሻ ወይም መለኪያ የሆኑትን ሕግጋት ትምህርት ላይ የተነሳውን ማለትም ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረው ግንኙነት አለ እንደገናም ለባልጀራው የሚሰራው መኖሩን ባልንጀራም ሲባል ደግሞ ጌታችን በወንጌል እንዳስተማረው አብሮን የሚኖር ሁሉ መሆኑን በማንሳት ትምህርቱን መጀመር ይቻላል፡፡ ከዚያም ቅዱስ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ያስተላለፈውን ትምህርት(ሮሜ 13) ይህም ክርስቲያን የሀገርን ሕግ አክብሮ በመሥራት ለሀገሩ ጥሩ ዜጋ በመሆን አስተዋጽኦ ማድረግ እንዳለበት በማብራራት ለውይይት መነሻ የሚሆን ሀሳብ ተማሪዎቹን ማስጨበጥ ጠቃሚ ነው፡፡ ከዚያም የሚከተለውን ጥያቄ ጠይቀው ተማሪዎቹ እርስ በራሳቸው እንዲወያዩበት ያድርጉ፤** • **አንድ ክርስቲያን ለሚኖርበት ማኅበረሰብ ወይም ሀገር ሊያበረክት የሚገባው ነገር ምንድነው?** **ለነዚህ ጥያቄዎች ተማሪዎች የሚሰጡዋቸውን መልሶች ተቀብለው መልስ ሳይሰጡ ወደሚቀጥለው ርዕስ ይሸጋገሩ፡፡**

የሚጠበቅ ብቃት/ /	ይዘት	የመማር ማስተማር ክንውን / / እና ዘዴዎች /ግብዓቶች
• በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ከክርስቲያን የሚጠበቁ የመልካም ምግባር ተግባራትን ያብራራሉ	7.2. በማኅበራዊ ሕይወት ከክርስቲያን ምን ይጠ በቃል • በጎ ሕሊናና ታማኝነት	ተማሪዎቹ የመለሱዋቸውን መልሶች አስታውሰው አንድ ክርስትያን በማኅበራዊ ሕይወቱ ሊኖረው የሚገባ ዋነኛ ነገሮች በጎ ሕሊናና ታማኝነት መሆናቸውን ጠቀሰው እነዚህን ነገሮች ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት አድርገው ምን ማለት እንደሆኑና መገለጫዎቻቸውን ይግለጹላቸው። ለምሳሌ ከአንድ ክርስቲያን የሚጠበቅ ቀዳሚ ነገር በጎ ሕሊናና ታማኝነት ሲሆን በጎ ሕሊና ማለት አንድ ክርስትያን በርሱም ሕይወት ይሁን በማንኛውም ሰው ሕይወት ውስጥ የሚሆነው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ለበጎ ያደረገለት እንደሆነ በማሰብ ነገሮችን በምስጋና የሚቀበልበት፤ ከሆነው ነገር ውስጥ ሁሉ ጥሩ ነገሩን ወይም መልካም ፍጻሜውን ተስፋ የሚያደርግበት፤ የሰዎችን ሀሳብና ንግግር ስሜትና ድርጊት በጥሩ ጎኑ ለመረዳት የሚጥርበት ወዘተ ማለት ነው። በጎ ሕሊና ያለው ሰው ነገሮችን አይመረምርም አያመዛዝንም ማለት ሳይሆን የሰዎች ድርጊት ክፉ ሆኖ እንኩን ሲገኝ በሥጋ ድካም ባለማወቅ ወዘተ መሆኑን በመረዳት ለማቅናት ለመደገፍ የሚሞክርበት መሆኑን እና የመሳሰለውን የበጎ ሕሊና መገለጫዎች ያብራሩላቸው። በሌላ በኩል በጎ ሕሊና ያለው ሰው ሰዎችን አይቀጣም ወይም አይቆጣም ማለት እንዳልሆነ ይልቁንም ለሰዎች በማሰብ ፍቅር ባልተለየው መንገድ በመቅጣትም ጭምር ሊያስተካክል የሚጥር ሊሆን እንደሚች ያብራሩላቸው። ታማኝነት ሰው ለተናገረው እና ቃል ለገባው ነገር ጸንቶ መስዋዕትነት እስከ መክፈል የሚደርስበት ወይም አምኖ ይቀርታ የሚጠይቅበት ሕሊና ነው። ይህንን በመሰለ መልኩ ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ በመጠኑ ካብራሩላቸው በሁዋላ የሚከተሉትን ሀሳቦች ያንሱላቸው፤ • በናንተ አመለካከት ታማኝ ነው የምትሉት ሰው ምን አይነት ሰው ነው? • በጎ ሕሊና ማለት ምን ማለት ነው? በነዚህ ሀሳቦች ዙሪያ ተማሪዎች እንዲወያዩ ካደረጉ በሁዋላ ለሚያነሱዋቸው ጥያቄዎችና ሀሳቦች ምላሽ ይስጡዋቸው።

• የራሳቸውን መንፈሳዊ ሕይወት ከተማሩት ትምህርት አንጻር በመገምገም የሚጠበቅባቸውን ለመሆን ጥረት ማድረግ ይጀምራሉ	• መልካም አርአያነትና ደግነት • ትህትናና ትጉህነት • ሰውን ሁሉ ማክበርና ቅንፍርድ	በዚህ ክፍለ ትምህርትም መልካም ርአያነትና ደግነት፤ ትህትናና ትጉህነት፤ ሰውን ሁሉ ማክበርና ቅንፍርድ ምን ማለት እንደሆኑ ያብራሩላቸውና የሚከተለውን የውይይት ሀሳብ ያንሱላቸው፡፡ • ለነዚህ ለተዘረዘሩት ሀሳቦች ጥሩ ምሳሌ ይሆናሉ የምትሉዋቸውን ሰዎች ከታሪክ ወይም ከቅዱሳት መጻሕፍት ወይም ከምታውቁት ከነምክንያቱ ጥቀሱ • ዛሬ ካለው የውድድርና የብልጣብልጥነት ወዘተ ኑሮ አንጻር እነዚህን ነገሮች እያደረጉ መኖር እንዴት ይቻላል ይህንን ሀሳብ አንስተው ተማሪዎቹን እንዲወያዩ ያድርጉዋቸው፡፡ ከዚያም የሚሰጡትን ሀሳብ ተቀብለው በምክር ያጠቃሉት፡፡
• ቁሳዊ ሀብት ከክርስትና ሕይወትና አኗኗር አንጻር የሚኖረውን ጥቅምና ጉዳት ይለያሉ • ክርስትያን ቁሳዊ ሀብቱን አስተዳደር ይገልጻሉ፡፡ • በአግባቡ ለመጠቀም ይወስናሉ	7.3. ቁሳዊ ሀብትና ክርስትና	ይህንን ክፍለ ትምህርት ሲጀምሩ ሉቃ 16 ላይ ያለውን የአልአዛርና የነዌን ታሪክ አንብበው ወይም ተርከው ወይም ሌላ ተመሳሳይ ታሪክ አምጥተው ይንገሩዋቸውና የሚከተለውን የመወያያ ነጥብ ያንሱላቸው፡፡ • *አልዓዛር በአብርሃም እቅፍ እንዲገባ ያደረገው ድሃ መሆኑ ነዌን ወደ ሲኦል እንዲገባ ያደረገው ደግሞ ሀብታም መሆኑ ነውን?* • *ሀብታም ወደ መንግስተ ሰማያት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢፎለክ ይሻለዋል የሚለው ቃል ሀብት ለመንግስተ ሰማያት እንቅፋት እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ስለዚህም ገብታም መሆን አያስፈልግም ቢል አንድ ሰው እንዴት ታዩታላችሁ?* በውይይቱ ማጠቃለያ ቁሳዊ ሀብት በራሱ ሃጢአት አለመሆነን ነገር ግን • ቁሳዊ ሀብትን ለማግኘት ሃጢአትን መሥራት እንደማይገባው (መስረቅ መዋሸት ...) • ቁሳዊ ሀብትን ካገኘም በሁዋላ በአግባቡ መጠቀም (አሥራትን በማውጣት፤ ለነዳያን በመመጽወት፤ሀገርን በልማት እና ሥራ በመፍጠር በመጥቀም ...) በዚህም ዓለም በወዲያኛውም ዓለም ተጠቃሚ ሊሆ የሚችል መሆኑን

		• ቁሳዊ ሀብትን ለማግኘት በሥጋ ስራ ብቻ ተውጦ ከጸሎት ከአገልግሎት ጭራሽ መራቅ ምንም እንኩዋን ነገሩ በራሱ ሃጢአት ባይሆንም ውሎ አድሮ ሃጢአትን ለመሥራት የነፍስን ድካም ስለሚያመጣ መልካም ነገርን አውቆ አለመሥራት በራሱ ሃጢአትም ስለሆን ከዚህ መቆጠብ እንደሚገባ ያስረዱዋቸው።
• ሥራና ክርስትና እንዴት ተጣጥመው መጓዝ እንደ ሚችሉ ያብራራሉ • ስለ ሥራ የቤተክርስቲያን አስተምህሮ በመዳት ያደንቀሉ • ስለ ሥራ እና ክርስትያናዊ ሕይወት በመረዳት የራሳቸውን ሕይወት ይመረምራሉ፤ ለበለጠ ትጋትና ሥራ ይነሳሳሉ	7.4. ሥራና ክርስትና	ቅዱሳት ስለ ሥራ የሚያስረዱትን እና ቤተክርስትያን የምታምነውን በማስረዳት መጀመር ጠቃሚ ነው። ብዙዎች በዘመናችን ቤተክርስትያን ሥራን እንደማታበረታታ፤ ልመናንን እንደምታስፋፋ፤ በዓላትን ማክበር ከሥራ ጥላቻ ወይም ሥራን ካለመውደድ ጋር በማያያዝ ወዘተ የሚያነሱትን ሀሳብ መልስ ሰጥቶ ተማሪዎቹ ክርስትያናዊ የሆነ የሥራ ጠባይ እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል። ስለዚህም በቅድሚያ ልዑል እግዚአብሔር ሰንበትን ለዕረፍት ሲሰራ እርሱ ሥራ ሠርቶ መሆኑን መግለጽ ይገባል። ስለዚህ ዕረፍት ካለ ሥራ የሚቀድም መሆኑን ማስረዳት፤በቅዱስ ወንጌልም ጌታችን አባቱ እስከ ዛሬ ይሰራል እኔም እሰራለሁ እንዳለ እርሱ በአምላክነቱ አምላካዊ ሥራን ፍጹም ሰው በመሆኑ ደግም ከሃጢአት በቀር እንደ ሰው በምድር ላይ ኖሮ አርአያ እንደሆነና ከድካም ከሃኬት ተለይቶ በሥጋም በነፍስም ትጉህ መሆንን የሚገባ መሆኑን እንዳሳየን ያብራሩላቸው። ቅዱሳን ሐዋርያትም ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለው እንዳስተማሩና በሕይወታቸውም ይህንኑ እንዳሳዩን ይልቁንም ቅዱስ ጳውሎስ ቀን በማስተማር ሌሎት የራሱን ወጭ የሚሸፍንበትን ድንኩዋን እየሰፋ የኖረ መሆኑን እና ሌሎችንም የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ማስረጃ አድርገው ይግለጹላቸው። ከዚህም በሁዋላ በሚከተሉት ሀሳቦች ዙሪያ ያወያዩዋቸው። • ሥራ ያጣ መለኩሴ ቆብ ቀዶ ይሰፋል? የሚለውን አባባል እንዴት ትረዱታላችሁ? • ሥራና ክርስትና እንዴት ተጣጥሞ መጓዝ ይችላል? ተማሪዎቹን ካመልስ ከተቀበሉ በሁዋላ በቀሩት የመጨረሻዎቹ 5 ደቂቃዎች ማጠቃለያ በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃሉ።

ማጠቃለያ

የማጠቃለያው ዓላማ ተማሪዎች በእያንዳንዱ ርእስና ንዑስ አርእስት ሥር የተዘረዘሩትን የሚጠበቁ ብቃቶችና አጠቃላይ ዓላማዎች መጨበጣቸውን /ማሳካታቸውን/ ማረጋገጥ ነው። ይህንንም ለማረጋገጥ መምህሩ የተለያዩ የግምገማ ዘዴዎችን እንደ አስፈላጊነቱና አመቺነቱ እያየ መጠቀም ይገባዋል። በግምገማ ዘዴዎቹም መሠረት ተማሪዎች የደረሱበትን የዕውቀት፣ የአመለካከትና የክህሎት ለውጥ ደረጃ መዝኖ ተንትኖና አስተካክለውጠት መስጠተ የመምህረ ተግባር ነው ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ዝቅተኛ ውጤት የመጡ ተማሪዎችን በመለየት እገዛ የሚያኙበትን አመቺ መርሐ ግብር በማዘጋጀት ወደ ሚጠበቀው የዓላማ ስኬት ማድረስና ብቃታቸውን ማረጋገጥ መምህሩ ተግባርና ሓላፊነት መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

የብቃት ዓይነቶች	በመርሐ ትምህርቱ የተቀመጡ ብቃቶች	የማስተማሪያ ዘዴዎች
አዕምሮአዊ ብቃቶች	ይገልጻሉ	የጽሑፍ ምዘና አጭር መልሰ ስጥ፣ጻፍ
	ይዘረዝራሉ	የጽሑፍ ምዘና አጭር መልሰ ስጥ፣ጻፍ
	ያብራራሉ	የጽሑፍ ምዘና አጭር መልሰ ስጥ፣ጻፍ
	ያሳያሉ	የጽሑፍ ምዘና አጭር መልሰ ስጥ ክፍት ቦታዎችን ሙላ፣አዛምድ ምርጫ ጥያቄዎች
	ያስረዳሉ	የጽሑፍ ምዘና አጭር መልሰ ስጥ የቡድንና የግል ሥራዎች
	ይተርካሉ	የጽሑፍ ምዘና አጭር መልሰ ስጥ ጻፍ፣ ጥያቄዎች የግልና የቡድን ሥራዎች
	ይተረጉማሉ	የጽሑፍ ምዘና አጭር መልሰ ስጥ ጻፍ፣ ጥያቄዎች
	ይናገራሉ	የጽሑፍ ምዘና አጭር መልሰ ስጥ ጻፍ፣ ጥያቄዎች
	ይተነትናሉ	የጽሑፍ ምዘና አጭር መልሰ ስጥ ጻፍ፣ ጥያቄዎች የግልና የቡድን ሥራዎች
	ይጠቅሳሉ	የጽሑፍ ምዘና አጭር መልሰ ስጥ ጻፍ፣ ጥያቄዎች አዛምድና ምርጫ
	ይለያሉ	እዛምድ እውነት ሐሰተ ምርጫ ክፍተ ቦታ መሙላት
	ያነጻጽራሉ	የጽሑፍ ምዘና፣ አጭር መልሰ ስጥ፣ ጻፍ፣ አዛምድ ጥያቄዎች
	ያቀርባሉ	የጽሑፍ ምዘና፣ አጭር መልሰ ስጥ፣ ጻፍ፣ አዛምድ ጥያቄዎች
የአመለካከት ብቃቶች		
	ያድንቃሉ	መጠይቅ፣ ጥያቄና መልሰ የግልና የቡደን ሥራዎችን
	ያስተካክላሉ	መጠይቅ፣ ጥያቄና መልሰ የግልና የቡደን ሥራዎችን
	ይመራሉ	መጠይቅ፣ ጥያቄና መልሰ የግልና የቡደን ሥራዎችን
	ይገመግማሉ	መጠይቅ፣ ጥያቄና መልሰ የግልና የቡደን ሥራዎችን